በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከፌብርዋሪ 21-29 እና ከማርች 01-10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ...... - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ...... - 3 -

ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...... - 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ...... - 3 -

ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ...... - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ ...... - 3 -

የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ...... - 3 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ...... - 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...... - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...... - 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ...... - 5 -

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...... - 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ...... - 6 -

ሁኔታ ትንበያ ...... - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-29, 2024 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ...... - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-29, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠንና ስርጭት በሚ.ሜ...... - 7 -

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ ...... - 7 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከማርች 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ...... - 8 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ...... - 8 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ...... - 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ  የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግበዋል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 3.4፣ 3.1፣ 8.2 እና 13.1፤ በአርባ ምንጭ 1.7፤ በሀዋሳ 13.6 እና 1.0፤ በኮምቦልቻ 6.2፤ በቢሾፍቱ 6.2፤ በጎሬ 9.4 እና 6.2፤ በጅማ 6.9፣ 6.4፣ 1.8 እና 5.6፤ በመተሃራ 4.0፣ 13.8፤ በነቀምቴ 1.3፤ በባሌ ሮቤ 9.8፤ በአቦምሳ 20.0፤ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 14.0፣ 1.4፣ 2.0 እና 9.2፤ በሀሮማያ 1.3፤ በአማን 8.5፣ 2.0፣ 10.0፣10.9 እና 8.3፤ በአምባ ማሪያም 3.7 እና 2.4፤ በአምቦ 7.0 እና 7.7፤ በአሊያ 7.9፤ በአርጆ 2.4፣ 8.6 እና 18.4፤ በአርሲ ሮቤ 4.0 እና 1.1፤ በአፅቢ 5.0፤ በአዋሽ አርባ 2.0፣ በበደሌ 11.2 እና 6.6፤ በብላቴ 2.0፣ 13.6 እና 5.2፤ በቦሬ 8.5 እና 5.0፤ በቡኢ 6.0 እና 8.6፤ በቡሬ 9.8 እና 7.6፤ በቡርጂ 2.5፣ 4.7፣ 1.9 እና 9.8፤ በጨፋ 8.5 እና 3.5፤ በጭራ 4.4፣12 እና 1.6፤ በደብረ ብረሃን 4.5፣ 19.8፣ 12.8 እና 3.2፤በደብረ ታቦር 2.2፤ በደብረ ወርቅ 11.1፣9.2 እና 11.5፤ በደምቢ ዶሎ 9.5፤ በዲላ 8.2፤ በኢጃጂ 12.2፣ 3.2፣ 3.8፣ 16.2 እና 4.5፤ በፍቼ 11.7 እና 3.8፤ በጋቲራ 15.7፣ 7.6 እና 13.6፤ በጋምቤላ 5.6፤ በግዮን 31.4 እና 10.0፤ በጉንዶ መስቀል 1.8፣ በቡሌ ሆራ 12.2፤ በሆሳዕና 4.9፣ 1.1፣ 15.3፣ 3.0 እና 1.8፤ በእምድብር 14.4፣ 5.5 እና 3.3፣ በጂንካ 8.2፣ 10.2፣ 7.5 እና 3.4፤ በካቺሴ 16.8፣ 5.8 እና 2.3፤ በኮንሶ 6.0፤ በቁሉምሳ 49.7 እና 14.0፤ በላይበር 2.6፤ በሊሙገነት 6.1፣ 10.6፣ 1.5፣ 7.9 እና 4.9፤ በማጀቴ 28.4፣ 8.8 እና 1.0፤ በማጂ 50.0፣ 10.5 እና 3.0፤ በመሃል ሜዳ 3.9፣3 .6 እና 6.0፤ በመካነ ሰላም 3.9፤ በሞጣ 2.1 እና 1.4፤ በንፋስ መውጫ 3.1 እና 1.2፤ በኑራኤራ 3.2 እና 4.3፤ በሳዉላ 6.2፣6.5 እና 18.8፤ በሰኮሩ 13.3 እና 3.5፤ በሰንቃጣ 10.0፣ በሻምቡ 1.9 እና 13.9፣ በሾላ ገበያ 3.3፣ 1.4፣ 4.5 እና 18.5፤ በሲርንቃ 6.3፣ 1.6፣ 13.0 እና 49.4፤ በቴፒ 3.5፣ 1.6፣ 1.7፣2.2 እና 7.5፤ በተርጫ 6.0፣ 10.7፣ 3.2 እና 1.9፤ በወገልጤና 2.2፤ በወራቤ 11.9 እና 10.7፤ በወላይታ ሶዶ 6.0 24.1፤ በየትኖራ 14.0 እና 2.6  እንዲሁም በባቱ 5.0 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር እና ጅማ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ሰሜን ወሎ፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ ምስራቅ ጎጃም እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ሁሉም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወላይታ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ እና የኮንታ ዞኖች ላይ ከ21-70 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-7 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ ዋህግምራ፣ ደቡብ ወሎ እና ምዕራብ ጎጃም ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፤ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 4፣ 2፣ 1፣ 5 እና 3 ፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ መዕከላዊ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች እንድሁም ሀረሪ እና ድሬ ዳዋ ላይ ከ5-20 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ነበራቸው(ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር እና ጅማ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ ዞን፣ ሁሉም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳዉሮ፣ ካፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ምዕራብ ኦሞ  እና ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኙዋክ እና ኑዌር ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4፣ 5 እና እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፤ በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35-42.6 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ለበልግ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅት ለማድረግ፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎትን ለማሟላት፣ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን፤ በተለይም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምስራቅ የበልግ አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው የአፈር ውስጥ እርጥበት የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)፡፡




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 ድረስ
የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት መካከለኛው እና ምስራቃዊ አባይ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ እንዲሁም በላይኛው እና መካከለኛው ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበ እስከ እርጥበታማ መጠን አግኝተዋል፡፡ በተለይም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በጥቂት የመካከለኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም በታቸኛው ምስራቃዊ አዋሽና በላኛው ስምጥ ሸለቆ ንዑስ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በሚቀጥሉት ዘጠኝ ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአንጻራዊ ሁኔታ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲና አርሲ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ቡኖ በደሌ፣ ምዕራብ ጉጂና ጥቂት የቦረና ዞን፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፤ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የዋግህምራ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 1፣ ዞን 4፣ ዞን 3 እና ዞን 5፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የሲቲ እና ጥቂት የፋፈን ዞኖች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)።




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Daily maximum temperature(c) for 21-29 Feb 2024




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-29, 2024
የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

Total Rainfall (mm) for 21-29 Feb 2024





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-29, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠንና ስርጭት

## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የማርች አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከሩ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ፤ ምስረቅ፤ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (1-29 ሚ.ሜ) ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ አማራ፤ በደቡብ ምዕራብ እና በመካከለናው የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8) ፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከማርች 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ያገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል የበልግ ወቅት ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት፣ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ግብዓት ከወዲሁ በማዘጋጀት የሚኖረውን እርጥበት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 29/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

**በሚቀጥሉት ቀናት በመካከለኛው ዓባይ፣ የላይኛውና የመከካለኛው ኦሞ ጊቤ፣ የስምጥሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ የአየር ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡**



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et